# የግንቦቱን ወጥመድ፣ ትውልድ ይፍረድ

(ከነቅዓ ጥበብ፣ ግንቦት 1998 ዓ. ም.)

አምና የዛሬ አመት፣ በወርሃ የካቲት፣
ትንሽ በር ተከፍቶ፣ እንደልብ ለማውራት፣
ሁሉም ተነፈሰ፣ ብሶቱ ወጣለት፣
ወያኔም ወዳጁን፣ ጠላቱን ለየበት።

ግፍ ያንገፈገፈው፣ ሁሉም አመረረ፣
መፍራት መሽማቀቅ፣ በዋለበት ቀረ፣
ቀስቃሽ ቀሰቀሰ፣ ምሁር አስተማረ፣
ጋዜጠኛ ተች፣ ሀቁን አበጠረ፣
ተቃዋሚው ሁሉ፣ በጋራ ዘመረ፣
ወጣት አዛውንቱ፣ ባንድ ልብ መከረ፣
ገጠር ተከተማ፣ ህዝብ ተባበረ።

ሆኖም ግን፣ ኢግአዴግ ውስጡን እያሴረ፣
አለምን በሙሉ፣ ሊሸውድ ሞከረ፣
ታዛቢን ጋበዘ፣ ቃሉን አሳመረ፣
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታን፣ እያመሳጠረ፣
እንከን እንደማይኖር፣ ደጋግሞ ፎከረ፣
ህዝቡ ግን ቀደመው
ወያኔን አዳክሞት፣ ወደ ሁዋላ ቀረ።

በመሬት አንቀጥቅጥ፣ የሰልፍ ማእበል፣
ኢህአዴግ ሰጠመ፣ ሜዳው ሆነ ገደል፣
እንደ ገሞራ እሳት፣ ህዝቡ ሲገነፍል፣
የወያኔ ካድሬ፣ ባንዳው የኮር አባል፣
አውደልዳዩ ሁሉ፣ በያለበት ቀጥኖአል።

ሰላማዊ ዜጋ፣ በሰላማዊ ሃይል፣
ማንነቱን ገልጡዋል፣ ያለማወላወል።

ያ ሰላማዊ ህዝብ፣ መቼ በሰልፍ ብቻ፣
በድምጥ ሲያጠቃም፣ ምንም የለው አቻ!

ቀንበሩን ለማውለቅ፣ ያለቅጥ ጎምጅቶ፣
ቁርስና ምሳውን፣ እራቱን እረስቶ፣
ተራውን ጠብቆ፣ እንቅልፉን ሰውቶ፣
ትንፋሹን ዋጥ አርጎ፣ በካርዱ አነጣጥሮ፣
በየመሸገበት ወያኔን ሰባብሮ፣
ባለመሳሪያውን በድምጽ ብቻ ጥሎአል፣
ግዳዩን በቀመር፣ ከምሮ አስመዝግቡዋል፣
ሀቅ አንድ ብቻ ናት፣ ማን ያስተባብላል!!?

ታዛቢ ባለበት፣ የጦር ግንባር ሁሉ፣
ህዝቡ አቸንፎ፣ ተደምድሙዋል ድሉ!

በዴሞክራሲ ስም፣ መሸንገል ሲፈልግ፣
ወያኔ ተረትቶአል፣ እርሱ ባወጣው ህግ፣
የሚሳነው የለም፣ ሰፊው ህዝብ ሲታደግ።

በአዲስ አበባ፣ በዋናው ከተማ፣
ለወያኔ ሞረሽ፣ ድምጽም አልተሰማ!
ታዛቢ ባለበት፣ የድምጽ ጣቢያ ሁሉ፣
ወያኔን ተፍቶታል፣ መራጩ በሙሉ፣
ታሪኩ ይሄ ነው፣ ቢወዱም ቢጠሉ፣
ህዝብ የጠላአቸው፣ እንዴት ያስጠላሉ!?

መለስም ሲናገር፣ ነገሩ ተሰምቶት፣
«ለምን ድምጻችሁን፣ ለእኛ ላለመስጠት፣
እንደወሰናችሁ፣ ገብቶናል በጽቅበት፣»
በማለት መስክሮአል፣ ሲናገር በምጸት።

ወዲያውም ቁርጡን ሲያቅ፣ ሂሳቡን ቀምሮ፣
ገና የምርጫው ካርድ፣ ሳያልቅ ተቆጥሮ፣
በሶስት መቶ ሃያ፣ ስድስትን ጨምሮ፣
«እኛ አሸንፈናል፣ ምርጫውን ዘንድሮ፣
ሰልፍ የሚባል የለም፣ ከዛሬ ጀምሮ፣
ጦሩም በእኔ ስር ነው፣ ሁሉም ተደምሮ፣
አንድ  ሰው እንዳላይ፣ እጣቱን ቀስሮ፣
የሰአት እላፊም አዋጅ፣ አውጥተናል፣
ወይ ትንፍስ! ወይ ንቅንቅ! ይኸው ተናግረናል።»
አለና ደስኩሮ፣ መለስ «ዴሞክራቱ!»
ዴሞክራሲን አንቆ፣ በህጻንነቱ፣
ትንፋሹን አጠፋው፣ ተለየ ህይወቱ።

አንዱ ሰው ፓርላማ፣ ብሄራዊ ሸንጎ፣
ሆኖ በመወሰን፣ ብቻውን ደንግጎ፣
ፍለጠው! ቁረጠው! የሚልበት አገር፣
በየት ይገኝ ይሆን?! ከኢትዮጵያ በቀር?!

ህዝቡን በጣም ንቆት፣ ባበጠው ትዕቢቱ፣
አፍህን ያዝ አለው፣ እንደልጅነቱ!
የእንከን የለሽ ምርጫ፣ ይህ ነው ምልክቱ!?

ግን የህዝብ ቁጣ፣ ብሶት ሲፈነዳ፣
በምን ይመረጋል?! መች ያጣል ቀዳዳ!
የኮረጆ ሌቦች፣ ድምጽን ሲሰርቁበት፣
እንደምን ይነሰው፣ ሌባ! ሌባ! ማለት?!

ያን የህዝብ ቁጣ፣ የነጻነት ብሶት፣
ተቃዋሚው ቢጥርም፣ በሰላም ለመፍታት፣
አሻፈረኝ ብሎአል፣ ወያኔ በእብሪት፣
«ከሌባ ጋር ጠበል፣ አትጠጡ» ቢሉ፣
ዘርን የሚያጠፋው፣ የቱ ነው ወንጀሉ?!

የወያኔ ትእቢት አልበርድ ስላለ፣
ከተማው በሙሉ፣ ባንድ ቀን ጸጥ አለ።

በወያኔ ስበከት፣ እንዳይዘናጉ፣
የታክሲ ሾፌሮች፣ በራቸውን ዘጉ፣
ሌሎቹም ተባብረው፣ ባሉበት መሸጉ።

ያለው ከሌለው ጋር፣ እየተካፈለ፣
ወቅቱን ለማሳለፍ፣ ድርሻውን ከፈለ፣
ክፉን ቀን ለማውጣት፣ ምን አማራጭ አለ!?

የወላጆቹን ድምጽ፣ ሌቦቹ ስለቀሙ፣
ተማሪ ተነሳ፣ ሊታደግ በደሙ፣
ዕጣ ፈንታው ሆኖ፣ ገና ከቅድሙ፤
ተማሪ ሲታፈን፣ ወላጅም ቢወጣ፣
አግአዚ የሚባል፣ ከጫካ የመጣ፣
ካውሬ የማይለይ፣ አረመኔ አይን አውጣ፣
በማንም ዜጋ ላይ፣ ደርሶ በማጉረጥረጥ፣
ባልቴት ሽማግሌ፣ ህጻናትን ሳይመርጥ፣
በጥይት በሰደፍ፣ በሳንጃ በቆመጥ፣
ሁሉንም አሰጣው፣ እንደ እንጨት በመፍለጥ፣
ያስር አመት ጨርቃ፣ እንቡጦች በመቁረጥ፤
እንደ ፋሽሽት ዘመን፣ ሁሉም ተወረረ፣
የግለሰቦች ቤት፣ ክብር ተደፈረ፣
በባል ሬሳ ላይ፣ የሚስት ተደመረ፣
ኢትዮጵያዊነት በኢትዮጵያ ቀረ!

የቅንጅትምን መሪዎች በሙሉ፣
የህዝብ ድምጽ ይከበር! ያሉትንም ሁሉ፣
ገብረው ከበሉ፣ ጥቂቶች በስተቀር፣
ከርቼሌ ላካቸው፣ በጨዋታው ሲያፍር፤
በዘር ማጥፋትና ሀገርን በመካድ፣
ከሃዲ ከሰሰው፣ ሁሉም አገር ወዳድ፣
አዬ ዴሞክራሲ!? ደላጎን በገመድ!!?

ምእራባዊያኑ ሀቁን አውቀውታል፣
ወኪሎቻቸውም ግፉን አይተውታል፤
ማን እንዳቸነፈ፣ በደንብ ያውቃሉ፣
ሀቁን ለመዋጥት ግን፣ ገና ያኝካሉ።
የህዝቡን ድል ክደው፣ ወያኔን አውቀዋል፣
ሀቁን ቢረዱትም፣ ሽንገላን መርጠዋል፣
«የድጎማ በጀት፣ ለመንግስት አንሰጥም፣
ለእኛ ወኪሎች ግን፣ ገንዘብ አንነፍግም፣»
በሚል አጉል ሽፋን፣ እያወላወሉ፣
አሁንም በዘዴ፣ ገና ያደባሉ።

«ልጅን ሲሳስሙ፣ ልጅን ሲያባብሉ፣
እስከነንፍጡ ነው» እንደሚባል ሁሉ፣
ወያኔ ኢህአዴግ፣ የስለት ልጃቸው፣
ጠልተው የማይጥሉት፣ ህጻን ሆኖባቸው፣
እስከለሃጩ ነው፣ መሳም የሚሻቸው።

መላው ቢጠፋቸው፣ ምን እንደሚያደርጉ፣
ተለጣፊን ፓርቲ፣ ለመፍጠር ፈለጉ፤
እነ አና ጎሜዝ በግልጽ ሲናገሩ፣
የምእራቡ ነገር፣ ብዙ ነው ምስጢሩ፣
ያዋዋላችን ውል፣ ድር ማግና ክሩ።

በዴሞክራሲ አለም፣ በጠፋበት ውሉ፣
የቁርጥ ቀን ልጆች፣ እስረኞች በሙሉ፣
ለጲላጦስ ችሎት፣ ይመላለሳሉ፣
መዳረሻቸውም ላመታት የጠፋ፣ ጭራሽ ያልታዩ አሉ፣
ፍርድ ከህዝብ ነው፣ በማን ይዳኛሉ!?
ትላንትን በዛሬ፣ ለሚያስተውል ሁሉ፣
ታሪኩ ይኸው ነው፣ እናንተስ ምን ትሉ?

የምርጫ ቦርድ መራጭ፣ በሆነበት አገር፣
አንዱ ሰው ፓርላማ፣ በሆነበት አገር፣
ሰላም ዴሞክራሲ፣ አይችልም ሊዳብር።

በህብረት በአንድነት፣ ወገኖች ታገሉ፣
«ነግ ለራሱ ያውቃል፣ ለነገ አትበሉ፣»
በረባ ባልረባው፣ አትከፋፈሉ፣
በግልጽ ተወያዩ፣ በፍቅር ተቻቻሉ፣
ለብሄራዊ እርቅ፣ መረዋ ደውሉ።

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.